## «መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም» ምን ማለት ነው?

***ኃይለ ገብርኤል - ከአራት ኪሎ***

የተከበራችሁ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆችና የዲ/ን ዳንኤል የጡመራ-መድረክ እድምተኞች ሰላመ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን።

ባለፉት ሳምንታት ወንድማችን ዲ/ን ዳንኤል በቤተ ክህነቱ ውስጥ ያሉትን፣የብዙዎቻችንን አንገት ያስደፉትንና አብዛኛው ምእመን በሆዱ ይዞ ዘወትር የሚያርበትንና የሚያለቅስበትን የቤታችንን ጉድ ዝምታ መፍትሔ አይደለም በማለት ብቻውን ነጥሮ ወጥቶ ከብዙ በጥቂቱ ለእኛ በሚገባን መልኩ ነግሮናል። ችግሮቹን ከመዘርዘር ባሻገርም መፈትሔ ሊያመጡ ይችላሉ ብሎ ያመነባቸውን ነጥቦችንም በግልፅ አመላክቷል።

እየበሉ እየጠጡ ዝም…… የሚለው የአበው ምሳሌ አንድም በኔ እንዳይተረት አንድም እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነቴ የድርሻዬን መወጣት ስላለብኝ  እነሆ በውስጤ ያለውን እናገር ዘንድ ጀመርኩ።

ዲ/ን ዳንኤል እንዳመለከተው በአሁኑ ወቅት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በተፈጠረው ችግር ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ይመለከተኛል የሚሉ ሁሉ በመነጋገር ላይ ናቸው፡፡ መፍትሔም ይሰነዝራሉ፡፡ ጠቅለል ተደርገው ሲታዩም የሚሰነዘሩት የመፍትሔ አቅጣጫዎች ሁለት መልክ አላቸው ***ተሐድሶ እና ትንሣኤ***። ተሐድሶ ተብዬው ለተፈጠረው ችግር በአንድም በሌላ ተጠያቂ እና ቢሳካለት ለቤተ ክርስቲያን ውድቀት ዘወትር የሚተጋ እንጂ ለሰላሟና አንድነቷ ተጨናቂ አይደለም። ስለዚህም በእኔ እምነት የመፍትሔው አቅጣጫ አንድና ብቸኛ ሲሆን እርሱም ***ትንሣኤ*** ነው። የትንሣኤን አቅጣጫ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉና በዲ/ን ዳንኤል የተመለከቱት ሁለት ጉዳዮች ደግሞ **አብርሖትና መዋቅራዊ ሽግግር** ናቸው። እነዚህ ሁለት መንገዶች መልካምነታቸው ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ ረዘም ያለ ጊዜን የሚጠይቁና የተራብነውን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት በቅርቡ ላይመልሱልን ይችላሉ ብዬ ሰጋሁ።

ስለዚህም እንደኔ አመለካከት ከአብርሖትና ከመዋቅራዊው ሽግግር ጎን ለጎን መንግስት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንዲወጣ ጠንከር ያለ ጫና ማሳደር ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ።

ይህ እምነቴ ግን መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም መባሉን ሳልሰማ ቀርቼ አይደለም። ከመስማትም አልፌ አንብቤዋለሁ ስለሆነም እስቲ ስለዚህ ጉዳይ የሚሰማኝን ልሰንዝር።

ሁላችንም እንደምናውቀው መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ይህም መሰረቱ በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሁለት አንቀፅ 11 ላይ የሰፈረው ነው። ይኸውም የሚከተለው ነው።

አንቀፅ 11 (የመንግስትና የሃይማኖት መለያየት)

1. መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።

2. መንግስታዊ ሃይማኖት የለም።

3. መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ አይገባም።

መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ማለት ግን ምን ማለት ነው?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እኮ የሀገሪቱ ብቸኛ የትምህርት ተቋም በነበረች ጊዜ ለራስዋም ሆነ ለሀገሪቱ የሚሆኑ፣ ምግባራቸው የቀና፣ አንደበተ ርቱዕ፣ በሰውና በእግዚአብሐር ዘንድ የተከበሩ፣ ሀገራችን ዛሬ ለደረሰችበት ስልጣኔ ፈር ቀዳጅ የሆኑ፣ በዓለማዊና መንፈሳዊ ዕውቀታቸው በሁለቱም ጎን እንደተሳለ ሰይፍ የሆኑ ሊቅና ሊቀ ሊቃውንትን በጥራት

ስታመርት የኖረች ናት። ይቺ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን ለማፍራት፣ የዕለት ተዕለት መንፈሳዊና ማሕበራዊ ተግባሮቿን ለማከናወን፣ ለቅዳሴው፣ ለማኅሌቱ፣ ለአቋቋሙ፣ ለሰዓታቱ፣ ለትርጓሜው፣ ለቅኔው፣ለድጓው የሚሆን የሰው ኃይል ራስዋ በራስዋ ማንንም ሳትለምንና ሳታስቸግር መሰረቷ በሆነው በልዑል እግዚአብሔር እርዳታ እና ዘወትር ደከመኝና ሰለቸኝ በማይሉና ለዓለም ሙት በሆኑ ልጆቿ ድካምና ጥረት ስታወጣ የኖረችና አሁንም በማውጣት ላይ የምትገኝ ናት።

ይህንን የተቀደሰ ተግባሯንም በሃገራችን ላይ በተለያዩ ዘመናት ስልጣን ጨብጠው ከነበሩ መንግስታት ጋር በመከባበርና በመረዳዳት እየሰራች ነፃነቷን ጠብቃ እነሆ በኢሕአዴግ ዘመነ መንግስት ላይ እንገኛለን። ታድያ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሰረቷ ፅኑ፣ተግባሯ መልካም፣ አላማዋና ግቧ እንደ ፀሐይ ጮራ ግልፅ፣ ፍሬዋም ለሀገራችን ሐዝቦችና መንግስትም ጭምር ጣፋጭ ሆኖ ሳለ መንግስታችን የሀጎች ሁሉ የበላይ በሆነው በህገ መንግስቱ ላይ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም በማለት በግልፅ ያሰቀመጠበት ምክንያት ምንድነው?

በእኔ አመለካከት መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ማለት፤

1. በተለያዩ የሹመት እርከን ላይ ያሉ የቤተክርስትያን አገልጋዮች ሹመታቸውና የመሿሚያው መስፈርት የሚወጣውና የሚፀድቀው በህገ ቤተ ክርስቲያን እንጂ በመንግስት አይደለም።

2. መንግስት በህገ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጁን በማስገባት ሰባቱን የአዋጅ አፅዋማት በዙ ብሎ መቀነስ አሊያም

አነሱ ብሎ መጨመር አይችልም።

3. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ያሬድ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጧትን ሶስቱን የዜማ አይነቶች

መንግስት እኔን ደስ አላሰኙኝም በማለት በማናቸውም መንገድ ማሻሻል ወይም መቀየር ፈፅሞ አይችልም አያስበውምም።

4. መንግስት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስርዓተ ቅዳሴ ጣልቃ በመግባት

ሀ. የፀሎተ ቅዳሴው ሰዓት ረዝሟልና አሳጥሩ ወይም አጠሯልና አስረዝሙ፣

ለ. ስትቀድሱ እንዲህና እንዲያ እያላችሁ ቀድሱ፣

ሐ. በሳምንት ይሔን ያህል በወርና በዓመትም ይህንና ያን ያህል ጊዜ ብቻ ቀድሱ፣

መ. ፀሎተ ቅዳሴ በእነዚህ ቀናት እንጂ በዚህና በዛኛው ቀን መፈፀም የለበትም፣

ሠ. በፀሎተ ቅዳሴ ጊዜ ተገኝተው ማስቀደስ ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እነ እገሌ እንጂ እነ እገሌ አይችሉም፣

ረ. በፀሎተ ቅዳሴ ጊዜ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገኘት ያለባቸውን የካህናትና የዲያቆናት እንዲሁም የምዕመኑ ቁጥር ይሄን ያህል ብቻ መሆን አለበት፣ ወዘተ... ብሎ መወሰን አይችልም።

5. መንግስት በቤተ ክርስቲያን ሙዳየ ምፅዋት ውስጥ ምዕመናንና ምዕመናት መጨመር ያለባቸው የገንዘብ መጠን

ቢያንስ ቢያንስ ይሔን ያህል ጣራው ደግሞ ይሄ ነው ብሎ ተመን ማውጣት አይችልም።

6. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በምትመራበት ቅዱስ መፅሐፍ ውስጥ ያሉትን ዓስርቱን ትዕዛዛት 9 ወይም 11 ማድረግ፣እንዲሁም አምስቱን አዕማደ ሚስጥራት 4 ወይም 6 ማድረግ፣ሰባቱን ሚስጥራተ ቤተ ክርስቲያንም 6 ወይም 8 ማድረግ አይችልም።

7. መንግስት በሚስጥረ ቁርባንም ያገባኛል በማለት ቅዱስ ቁርባንን መቀበል የሚችሉት ምዕመናንና ምዕመናት ሊያሟሉ ከሚጠበቅባቸው መንፈሳዊ መስፈርት በተጨማሪ ዲፕሎማና ዲግሪ ሊኖራቸው ይገባል፣ በፖለቲካ አመለካከታቸውም ጀርባቸው እየተጠና መሆን አለበት ብሎ መደንገግ ፈፅሞ አይችልም።

8. ምዕመናንና ምዕመናት ፀሎት ለማድረግ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱበትን ሰዓት፣ የሚፀልዩትን የፀሎት አይነት፣

የሚያነቡትን የፀሎት መፅሐፍ ዓይነት፣በፀሎት ሰዓት ስለሚኖራቸው እንቅስቃሴ መወሰን አይችልም።

9. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ህልውናዋን ይበልጥ በማጠናከርና ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በምታደርገው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ሐዋርያዊ ተልእኮዋን እንዳትወጣና ለታሪክና ለትውልድ የሚተላለፉ አበይት የሥራ ክንውኖችንም እንዳታስመዘግብ መንግስት በአንድም በሌላ መንገድ እንቅፋት መሆን ወይም መፍጠር የለበትም።

10. ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትናንት የነበረች ዛሬም ያለች ነገም የምትኖር ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ናትና ወቅቱ የሚጠይቀውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በሚገባ መወጣት ትችል ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራች የምታከናውናቸውን ክንዋኔዎች መንግስት ለእርሱ በሚመቸው መልኩ መቃኘት አይችልም።

ወዘተ… ማለት ነው እንጂ፤

1ኛ. ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ምንጭ ሆና የኖረች ቤተ ክርስቲያን መሆኗን፣

2ኛ. ከጥንት ጀምሮ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንደበቱን የሚፈታው መሠረታዊ የቋንቋና የሥነ ጽሕፈት ዕውቀት የሚያገኘው ከዚች ቤተ ክርስቲያን መሆኑን፣

3ኛ. ዘመናዊው ትምህርት በሀገሪቱ እስከተዘረጋበት ቅርብ ጊዜ ድረስ ጠቅላላው የትምህርት ቁልፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ እጅ ተይዞ የነበረ መሆኑን፣

4ኛ. የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ ብዙ ሊቃውንትን ሲያበረክቱ የኖሩ መሆኑንና አያበረከቱም መሆናቸውን

በመዘንጋትና እጇን አመድ አፋሽ በማድረግ ህፃናት በጥሩ ሰነ-ምግባር እንዲያድጉ፣ ብሔርና ብሔረሰቦች ተከባብረውና ተዋድደው እንዲኖሩ፣ በተለያዩ የመንግስት የኃላፊነት ቦታ ላይ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለስራቸውና ለህሊናቸው ታማኝ እንዲሆኑ፣ ምእመኑ ቀኑን ሙሉ በፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲውል፣ ምእመኑ በመንግስት አካላት በደል ቢደርስበት እንኳን ስሜታዊ ባለመሆንና ትዕግስትን ገንዘቡ በማድረግ ችግሮችን በህጋዊ መንገድ እንዲፈታ ከዚህም ካለፈ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ብሶቱንና መበደሉን ለእግዚአብሔር እንዲያሳውቅ፣ ወዘተ… በማስተማርና በመምከር ለሀገራችን ሕዝቦች እና ለመንግስትም ጭምር የዋለችውን ውለታ በመርሳት

1ኛ. ለብዙዎች ዓለማዊና መንፈሳዊ ጥበብን ዘወትር ሲመግቡ የኖሩትና በመመገብም ላይ የሚገኙት የቤተ ክርስቲያን ጡቶች እና እጆች በአጉራ ዘለል ግለሰቦች ሲነከሱ፣

2ኛ. ህዝበ ክርስቲያኑ ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲውል ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ በሙዳየ ምፅዋት የጨመረው ገንዘብ ሲመዘበር፣

3ኛ. ምዕመኑን በንፁህ ልቦና እና መልካም አርዓያነት የሚያገለግሉ አገልጋዮች መብት ሲነካ፣

4ኛ. ለዘመናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትተዳደርበት የነበረው ሕግ እና አስተዳደር ሲጠፋ፣

5ኛ. በቅድስት ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሀገሪቱን መልካም ገጽታ የሚያበላሽ ተግባር ሲፈጸም፣

6ኛ. ጥንታዊቷና ሐዋርያዊቷ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለ ሕዝቦቿ ሰላምና ፍቅር ዘወትር የሚያለቅሱት አገልጋዮቿ እየተገፉ በምትካቸው በቤተ ክርስቲያን ችግር የሚያተርፉ ሆዳቸው አምላካቸው በሆኑ ግለሰቦች ስትወረር፣

7ኛ. በቅድስት ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አይደለም ለቤተ ክርስቲያን ለሌላም የሚተረፍ መንፈሳዊ ጥበብና እውቀት ባለቤት የሆኑ አባቶች እያሉ የመንፈሳዊነትን ትርጉም እንኳን በቅጡ የማያውቁ ግለሰቦች ያልተገባቸውን መነፈሳዊ ስራ እንስራለን እያሉ ሲያበላሹት፣

8ኛ. በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ቦታዎች ቦታውን የማይመጥን መንፈሳዊነትና ዕውቀት የሌላቸው ገለሰቦች ተቀምጠው ህዝበ ክርስቲያኑ ከቦታው ሊያገኘው የሚገባውን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳያገኝ ሲደረግ፣ 9ኛ. በቤተ ክህነቱ ውስጥ ተቀምጠው ለሚያጠፉት ጥፋት ተጠያቂ ላለመሆን ራሳቸውን በአንድም በሌላ መንገድ ከመንግስት አካላት ጋር በማቆራኘት መንግስትን ለጥፋታቸው መሸፈኛና ተባባሪ በማድረግ ዘወትር በጥፋት ላይ ጥፋትን የሚጨምሩ፣ መንፈሳዊነትን ለዓለማዊ ጥቅም የሸጡ፣ የቤተ ክርስቲያንን ህግና ስርዓት ሲቆርጡና ሲቀጥሉ የሚውሉ፣ የክህነት ካባ የለበሱ ነገርግን ክህነት በውስጣቸው የሌለ፣ ክርስቲያን ነን የሚሉ የክርስቲያን ምግባር የሌላቸውና ህዝበ ክርስቲያኑን ከመንግስት ጋር ለማጋጨት ሌት ተቀን የሚተጉ ግለሰቦች ሲበራከቱ፣

10ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ለእምነታቸው ያላቸውን ክብርና ለቤተክርስቲያናቸው ያላቸው መንፈሳዊ ቅንዓት እስከ መስዋዕትነት መሆኑን እያወቁ ምእመኑ ከልጅነቱ ጀምሮ በውስጡ ያደገውን ጨዋነት፣ ህግ አክባሪነት፣ ሰላም ወዳድነት፣ ሆደ ሰፊነትና መንፈሳዊ ትዕግስትን በመፈታተን በውስጣቸው ሸሽገው ለያዙት ርካሽ ዓላማ መጠቀሚያ ለማድረግ ሲሯሯጡ፣መንግስት በቸልታ ማየት አለበት ማለት አይደለም፡፡

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ሲደፈርስ አስችሎት በቸልታ ማየት አለበት ማለት አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ለማቃጠል የሚለኮሰው እሳት መንግስት እርሱንም እንደማይምረው ጠንቅቆ ያውቀዋል።

ስለዚህ የተከበራችሁ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች በአሁኑ ሰዓት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የተፈጠረውንና የብዙዎቻችንን አንገት ያስደፋውን ችግር በጊዜያዊ ማስታገሻ ሳይሆን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከነ ሰንኮፉ ለማስወገድ መንግስት ኃላፊነቱን ሊወጣበት ስለሚችልበት መንገድና ሊወስዳቸው ስለሚገባቸው የማስተካከያ እርምጃዎች በግልፅ እንነጋገር።

***"የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር ያከናውንልናል እኛ ባሪያዎቹም ነስተን እንሰራለን" ነህምያ 2፡20***

ቸር ያሰማን።